መልእክት ሁለት

## በባሕላችን ፈንታ ሁሉን-ያካተተውን፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስን መኖር

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤፌ. 3፡11፣ 16-17፤ ፊልጵ. 1፡20-21፤ ቆላ. 1፡15፣ 18፣ 27፤ 3፡4፤ 10-11

**I. የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊው ሃሳብ የክርስቶስ አካል፣ አንዱ አዲሱ ሰው ለሆነችው ቤተ-ክርስቲያን ክርስቶስን እንድንኖር እግዚአብሔር መፈለጉ ነው—ፊልጵ. 1፡21፣ ኤፌ. 2፡15-16፦**

ሀ. የእግዚአብሔር ውጥን ክርስቶስን እንኖረው ዘንድ በክርስቶስ ሙሉ በሙሉ እንድንሞላ፣ እንድንሰረግ፣ ሙሉ እንድንሆን እና ክርስቶስን እንድንለብሰው ነው—ኤፌ. 3፡17፣ ገላ. 2፡20፣ 3፡27፣ 4፡19።

ለ. የክርስትና ሕይወት የክርስቶስ አማኞች ክርስቶስን የሚኖሩበትና የሚያጎሉበት ሕይወት ነው—ፊልጵ. 1፡20-21።

ሐ. ክርስቶስን መኖር ማንነትን፣ ክርስቶስ ራሱን መኖር ነው—ቆላ. 1፡27፣ ሮሜ. 8፡10፦

1. ክርስቶስን ለመኖር እርሱን እንደማንነታችን መውሰድ እና ከእርሱ ጋር አንድ ማንነት መሆን አለብን። እርሱ እና እኛ ተግባራዊ በሆነ መንገድ አንድ መሆን አለብን—1ቆሮ. 6፡17።
2. ክርስቶስ በየዕለት ኑሯችን ምን ያህል በሌሎች ነገሮች እንደተተካ ብርሃኑ ካለን፣ እርሱን ከመኖር ይልቅ ሌሎች ብዙ ነገሮችን እንደምንኖር፣ ከክርስቶስ ይልቅ በባሕል የበለጠ እንደምንኖር ለጌታ እንናዘዛለን—1 ዮሐ. 1፡7።

መ. ክርስቶስን የማንኖርበት ምክንያት በክርስቶስ ስላልተቀናበርን ነው፤ የምንኖረው ነገር የተቀናበርንበትን ነገር ነው—ቆላ. 3፡4፣ 10-11፤ ኤፌ. 3፡17።

**II. ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ ከባሕል ተፃራሪ የመሆኑን ጉዳይ በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለው ሙሉ መገለጥ መሠረት የእግዚአብሔር ውጥን ወደ ተመረጡት፣ ወደ ተዋጁትና ዳግም ወደ ተወለዱት ሕዝቡ ውስጥ ራሱን በክርስቶስ መሥራት መሆኑን ማየት ያስፈልገናል—ገላ.1፡15-16፤ 2፡20፤ 4፡19፦**

ሀ. በአጽናፍ-ዓለም፣ በዘመናት እና በትውልዶች ሁሉ የእግዚአብሔር ማዕከላዊ ሥራ፣ ልዩና-ብቸኛ ሥራው ራሱን በክርስቶስ ወደ ተመረጡት ሕዝቡ ውስጥ መሥራትና ራሱን ከእነርሱ ጋር አንድ ማድረግ ነው—ኤፌ. 3፡17፤ 1 ቆሮ. 6፡17።

ለ. የእግዚአብሔር ውጥን ራሱን የውስጥ ንጥረ-ነገሮቻችን በማድረግ ጥልቅ-ዝርዝር በሆነ መንገድ ራሱን በክርስቶስ በእኛ ውስጥ መሥራት ነው—ኤፌ. 3፡11፣ 16-19።

ሐ. ለዘላለማዊ ኢኮኖሚው መፈጸም በሕይወትና በባህሪይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔር ሊያደርገን እንደ ሕይወታችን፣ ተፈጥሮአችንና ቅንብራችን ራሱን በክርስቶስ ወደ እኛ ውስጥ በመገንባት እግዚአብሔር በክርስቶስ ራሱን ወደ ማንነታችን ውስጥ መገንባት ይፈልጋል—2ሳሙ. 7፡12-14፤ ሮሜ. 1፡3-4፤ ኤፌ. 3፡17፤ ዮሐ. 14፡23፤ ቆላ. 3፡10-11፦

1. መላው ማንነታችን እንደገና በክርስቶስ እንዲቀናበር እግዚአብሔር በክርስቶስ ራሱን ወደ ውስጠ-መሠረታዊ ቅንብራችን ውስጥ ሊገነባ ያስፈልገናል—ኤፌ. 3፡17።
2. ክርስቶስ ወደ መንፈሳችን በመምጣትና መላው ነፍሳችንን ለመያዝ ከመንፈሳችን ወደ አእምሯችን፣ ስሜታችንና ፈቃዳችን በመሰራጨት ቤተ-ክርስቲያንን ይገነባል—ማቴ. 16፡18፤ ኤፌ. 3፡17።

**III. ክርስቶስ ከባሕል በተፃራሪ ነው በማለታችን ባሕላችንን መጣልና ምንም ይሁን ምን ከማንኛውም ባሕል ውጪ መኖር አለብን እያልን አይደለም—ቆላ. 3፡10-11፦**

ሀ. ክርስቶስ የሌላቸው በእርግጥ በባሕል መሠረት መኖር ያስፈልጋቸዋል፣ ምክንያቱም ባሕል ሰዎችን ይጠብቃል፣ ይቆጣጠራል ያሻሽላማል።

ለ. ሁሉም ሰው ሁሉን ያካተተውን፣ ሁሉን ደረስ የሆነውን ክርስቶስን ከመቀበሉ በፊት ባሕል ያስፈልገዋል።

ሐ. ክርስቶስን ከተቀበልን በኋላ ባሕል ክርስቶስን እንዲገድበው ወይም ክርስቶስን ከመለማመድና ከመደሰት እንዲያስተጓጉለን መፍቀድ የለብንም፤ ይልቁንም በባሕል መሠረት ሳይሆን በክርስቶስ መሠረት መኖርን መማር አለብን—2፡6-7።

መ. ልጆች እያደጉ ሲሄዱ ባሕልና ሕግ ያስፈልጋቸዋል—ገላ. 3፡23-28፦

1. ልጆች ክርስቶስን ከመቀበላቸው በፊት በባሕል መሠረትና ከሕግ በታች መሰልጠን አለባቸው—ቁ. 23-24።
2. ክርስቶስን ከተቀበሉ በኋላ ቀስ በቀስ ከባሕል ወደ ክርስቶስ እንዲዞሩ ልንረዳቸው እንችላለን—ዮሐ. 1፡12-13፣ 6፡57።

**IV. እኛ ክርስቶስን ስለተቀበልን ባሕል ለእርሱ ምትክ እንዲሆን መፍቀድ የለብንም—ቆላ. 2፡6፣ 3፡10-11፦**

ሀ. ሁሉም አይነት ባሕል ከክርስቶስ በተፃራሪ ነው፣ ክርስቶስም ከሁሉም አይነት ባሕል በተፃራሪ ነው—ቁ.11፡-

1. እያንዳንዱ ባሕል ምንም አይነት ባሕል ቢሆን ከክርስቶስ በተፃራሪ ነው።
2. ያለ ክርስቶስ ያለን ነገር ሁሉ እና እንዳንዱ የስብዕና ፍሬ እና መዳበር የባሕል ክፍል ነው።

ለ. የክርስቶስ ድሰታችንን መስፋት የሚገድበው ምክንያት ባሕል ነው፤ በውስጣችን ያለው ባሕል እውነተኛ ከሆነው የክርስቶስ ልምምድ ቅጽበታዊ በሆነ መልኩ ይገድበናል—ፊልጵ. 3፡3-9።

ሐ. ባሕል ክርስቶስን ከመለማመድ፣ ከመደሰትና ከመኖር ስለሚከለክለን በጌታ ምለሳ ያሉ ቅዱሳን ሁሉ ተግባራዊ በሆነ መንገድ ባሕላቸውን ለመተካት ክርስቶስን እንደ ሕይወታቸውና ማንነታቸው መውሰድ እንዲማሩ ጌታ ከባድ የሆነ ሸክም ሰጥቶናል—ኤፌ. 3፡17፤ ቆላ. 3፡4።

መ. ጌታን ለመደሰት አቅማችንን እንድናሳድግ ባሕላችንን ለመተው በክርስቶስ ነፃነት አለን፤ በውስጣችን ያለው ሁሉም ክፍል ለክርስቶስ መሰጠት አለበት።

ሠ. በውስጣችን ያለው አቅም በሙሉ ለክርስቶስ ከቀረበ፣ ቅጽበታዊ በሆነ መልኩ በውስጣችን ያለው ባሕል በውስጣችን በሚያድረው ክርስቶስ ይተካል—1፡27፣ 3፡11።

## V. የክርስቶስን ሁሉን-አካታችነት እና ሁሉን-ደረስነት ራእይ ማየታችን ወሳኝ ነው፤ እንደዚህ ካለው ራእይ ውጪ ባሕላችንን ለመጣል መጣጣር የለብንም—ሐዋ. 26፡19፤ ኤፌ. 1፡17-23፡-

ሀ. በውስጣችን የሚያድረው ክርስቶስ ትንሽ፣ የተገደበ ክርስቶስ አይደለም፤ እርሱ የማይታየው አምላክ ምሳሌ፣ የእግዚአብሔር ሙላት አካል መልበስ እና የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ትኩረታዊ ነጥብ ነው—ቆላ. 1፡15፣18፤ 2፡2፣ 9-10።

1. እንዲህ ያለው ክርስቶስ አሁን በውስጣችን ይኖራል እናም በመላው ማንነታችን ውስጥ ለመሰራጨት እድል እየጠበቀ ነው—1፡27።
2. ይህ ክርስቶስ በየዕለት ኑሯችን ሁሉ ነገር መሆን አለበት፣ እኛም በኑሯችን ለባሕል ምንም ስፍራ ባለመስጠት እርሱን መኖር አለብን—ፊልጵ. 1፡21፤ ቆላ. 3፡11።

ለ. ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነውን ክርስቶስን ራእይ እንዳየን፣ ባሕላዊ መነሻ ታሪካችንን ወደ ጎን መተውና ክርስቶስን እንዲተካው ወይም እንዲገድበው መፍቀድ የለብንም—ሐዋ. 9፡4-5፤ 26፡19፤ ፊልጵ. 3፡7-10፡-

1. በኑሯችን ለባሕል ምንም ስፍራ መስጠት የለብንም።
2. ይልቁንም በውስጣችን ያለው ሁሉም ክፍል በውስጣችን ለሚያድረው ሁሉን-ላካተተው፣ ሁሉን-ደረስ ለሆነው ክርስቶስ መሰጠት አለበት—ቆላ. 1፡27።

ሐ. በውስጣችን የሚያድረው ሁሉን-ያካተተውን፣ ሁሉን-ደረስ የሆነውን ክርስቶስ ራእይ ካየን፣ ቅጽበታዊ በሆነ መንገድ ባሕላችንን እንተዋለን—3፡10-11፡-

1. ቀድሞ ክርስቶስ በባሕል ተተክቶ ነበር አንዴ ይህንን ራዕይ ካየን ግን በውስጣችን ያለው ባሕል በክርስቶስ ይተካል—ቁ. 11።
2. ባሕላችንን ለመተው በመሞከር ፈንታ ክርስቶስን መኖር አለብን፣ ክርስቶስም ባሕላችንን በራሱ ይተካዋል—ፊልጵ. 1፡21።

መ. ክርስቶስን ስንኖር፣ ቅጽበታዊ በሆነ መንገድ ከባሕል አርነት እንወጣለን፣ የምንኖርበት ክርስቶስ ከሰው ቁጥጥር ወጪ በሆነ መንገድ ባሕላችንን ይተካል፤ ይህ በቆላስይስ መጽሐፍ ያለው መገለጥ ነው—1፡15፣ 18፣ 27፤ 2፡2፣ 9-10፤ 3፡4፣ 10-11።

© 2020 Living Stream Ministry